

# የአባ ሠንጋ በሽታ

የአባ ሠንጋ በሽታ ከእንስሳት ወደ ሰዎች ተላላፊ የሆነ አደገኛ በሽታ ነው፡፡


MINISTRY OF AGRICULTURE
ETHIOPIA
USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE
JOHNS HOPKINS
Center for Communication Programs


## ሀ. የአባ ሠንጋ በሽታ ምንነት

- በበሽታው የተያዙ እንስሳት ወይንም ሰዎች በወቅቱ ተገቢውን ህክምና ካላገኙ ለከፍተኛ ህመም ወይንም ሞት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡
- በሽታው በዋናነት ሣር የሚግጡ እንስሳትን ያጠቃል። የአባ ሠንጋ በሽታ በአብዛኛው ከመጋቢት አንስቶ እስከ ክረምት መግቢያ ባሉት ወራት ይከሰታል።

## ለ. የአባ ሠንጋ በሽታ ምልክቶች

### 1. በእንስሳት ላይ

- የአባ ሠንጋ በሽታ መንስኤ የሆነው ተሕዋስ በተፈጥሮ በአፈር ውስጥ ቢኖርም ሳይቀሰቀስ ለረዥም ጊዜ ሊቆይ ይችላል፤
- በሽታው ሲከሰት በተወሰነ ቦታ ወይንም አካባቢዎች እንስሳት በአብዛኛው በድንገት ይሞታሉ፤ በበድኑ ቀዳዳዎች (አፍንጫ፣ እፍ፣ ፊንጢጣና የመሣሰሉት) በኩል የማይረጋ ደም መፍሰስ ዋነኛው የበሽታው መገለጫ ምልክት ነው፤
- አንዳንድ እንስሳት ደግሞ ከመሞታቸው በፊት የሚከተሉትን ምልክቶች ሊያሳዩ ይችላሉ፤
  - ለመጋጥ ወይንም ለመጠጣት መቸገር፣
  - ለመተንፈስ መቸገር፣
  - አንገታቸው አካባቢ እብጠት ሊታይባቸው ይችላል።




### 2. በሰዎች ላይ

- በበሽታው ከተያዙ ወይንም ከሞቱ እንስሳት ጋር ንክኪ ከተደረገ ንክኪው በተፈጠረበት የቆዳ አካባቢ ህመም ያለው ቁስለት መከሰት፤
- የመተንፈሻ አካላት መታወክ ምልክቶች፣ ማለትም ትኩሳት፣ የደረት ላይ ህመም፣ ድካም እና ደረቅ ሳል ከምልክቶቹ ውስጥ ሊሆኑ ይችላሉ፤
- የአንጀት መታወክ ምልክቶች እንደ ማቅለሽለሽ፣ ትውከት፣ ትኩሳት እና የአንጀት መድማትም ሌሎቹ ምልክቶች ናቸው።



## ሐ. የአባ ሠንጋ በሽታ የመተላለፊያ መንገዶች

- በአባ ሠንጋ በሽታ አምጪ ተዋስያን ወይንም ባክቴሪያ የተበከለን ሥጋ እና የእንስሳት ውጤቶች ጥሬያቸውን ወይንም በአግባቡ ሳያበስሉ መመገብ
- በባክቴሪያው ከተበከለ/ከተነካካ ቆዳ/ጸጉር፣አጥንት እና ሌሎች ፈሳሾች ጋር ንክኪ መፍጠር
- በአባ ሠንጋ በሽታ የሞተ እንስሳ ቆዳና ፀጉር ላይ የሚገኝ ብናኝ ወደ ሳንባችን ሲገባ



የአባ ሰንጋ በሽታ መተላለፊያ ዑደት

## መ. የአባ ሠንጋ በሽታ የመከላከያ መንገዶች

- በአካባቢው ያሉ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች በሚያወጡት መርሀ ግብር መሠረት እንስሳትን ማስከተብ፣
- የታመሙ ወይንም የሞቱ እንስሳትን ሥጋ ለእርድ ወይንም ለቅርጫ አለማቅረብ ሥጋውንም አለመመገብ፣
- የታመሙ ወይንም የሞቱ እንስሳትን ተገቢ መከላከያ ሳያደርጉ ወይንም በባዶ እጅ አለመንካት፣
- ያልበሰለ ወይንም ጥሬ ሥጋ አለመብላት፣
- በአባ ሠንጋ በሽታ የሞቱ እንስሳትን ቆዳ ለማንኛውም አገልግሎት አለመጠቀም፣
- በአባ ሠንጋ በሽታ የሞቱ እንስሳትን በድን በባለሙያ ምክር ታግዞ በአግባቡ መቅበር ወይንም ማቃጠል፤

## እንስሳት ሲታመሙ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች፤

1. የታመሙ እንስሳትን ከጤነኞች መለየት፣
2. በአቅራቢያ ለሚገኝ የእንስሳት ጤና ባለሙያ ወይንም ለጤና ኤክስቴንሽን ወይንም ለቀበሌ አስተዳደር ወዲያውኑ ማሳወቅ፣
3. በአካባቢው ያሉ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች በሚያወጡት መርሀ ግብር መሠረት እንስሳትን ማስከተብ፣
4. የታመሙ እንስሳትን ለእርድ ወይንም ለቅርጫ አለማቅረብ ሥጋቸውንም አለመመገብ፣
5. የታመሙ እንስሳትን ተገቢ መከላከያ ሳያደርጉ ወይንም በባዶ እጅ አለመንካት፣

## እንስሳት ሲሞቱ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች፤

1. በድኑን ተገቢ መከላከያ ሳያደርጉ ወይንም በባዶ እጅ አለመንካት፣
2. የሞተውን እንስሳ ቆዳ ለማንኛውም አገልግሎት አለመጠቀም፣
3. የሞቱ እንስሳትን በድን በባለሙያ ምክር ታግዞ በድኑ ሳይከፈት በአግባቡ መቅበር ወይንም ማቃጠል፤
4. የመቅበሪያ ቦታው ከውሃ መገኛ፣ ከግጦሽ፣ ከእርሻ እና ለሌሎች አገልግሎች ከሚውሉ ቦታዎች የራቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣
5. ከእንስሳት ጋር ከሚደረግ ማንኛውም ንክኪ በኋላ ወዲያውኑ እጅን በውሃና ሳሙና መታጠብ